# በደም ቀለም የተፃፈ ቃል ኪዳን

በኃይሉ ቁምላቸው

ዜጎች ኑሮአቸውን እንዴት እንደሚገፉ የተቸገሩበት፣ ተስፋቸው ተሟጥጦ ግራ የተጋቡበት፣ መቋጫ በሌለው ጦርነት፣ ረሀብና ስደት የሚንገላቱበት ያ ወቅት ዳግም ላይመለስ ሄዷል፡፡

ዜጎች ዛሬ ለአዲስ ሕይወት ማበብ ተስፋ ሰንቀው ኑሮን ማጣጣም ይዘዋል፡፡ ሠላማዊ አየር መማግ፣ ሰርቶ መግባትና በነፃነት መንቀሳቀስ ችለዋል፡፡

ለዚህ መብቃት የተቻለው ደግሞ ሺህዎች በከፈሉት የሕይወት መስዋዕትነት በተገኘው ዴሞክራሲያዊ ሂደት ነው፡፡ ጨቋኝ አምባገነናዊ ሥርዓት ተገርስሶ በሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ የመንግሥት ሥልጣን የሚረከቡበት አገር መፍጠር ተችሏል፡፡

በረዥም ጊዜ የነፃነት ታሪኳ፣ በጥንታዊ ሥልጣኔዋ፣ በጥልቅ የመቻቻል ባህሏ የምትታወቀው ኢትዮጵያ ከሕዝብ በሚገኝ ድምፅ በምርጫ አሸንፎ መንግሥት የመመሥረት እድል ካጋጠማት ሁለት አሥርተ ዓመታት ሆኗታል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ የጀመሩት ይህ ጉዞ አዝጋሚ እንዳይሆን ብሎም ሂደቱ እንዳይነጥፍ አሊያም እንዳይቀለበስ ቃል ኪዳናቸውን በሕገ መንግሥቱ አስረዋል፡፡

ትናንት በአገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሚቆጠሩ ሕዝቦች፤ አካባቢያቸውም በፀባይ ማረሚያነት ተፈርጀው የልማት ተቋዳሽ መሆን ያልቻሉ ክልሎች እንደነበሩ ማስታወሰ ይገባል፡፡

የተጎናፀፉትን ሠላምና ዴሞክራሲ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከልማቱ በፍትሃዊነትና እኩልነት ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ የፀና እምነት ተይዟል፡፡ ውጤቱንም ማጣጣም ጀምረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሚያዝያ 21 ቀን 1998 ዓ.ም በአንድ ጉዳይ ላይ መክሮ ውሣኔ አሳልፏል፡፡ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ዋስትና የሆነው ህገ መንግሥት የፀደቀበት ህዳር 29 ቀን በየዓመቱ በተለያዩ ዝግጅቶች እንዲከበር፡፡

ይህንኑ መነሻ በማድረግ ህዳር 29 የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በመላ አገሪቱ በተለያዩ ዝግጅቶች መከበርን ይዟል፡፡

ዘንድሮም ለስድስተኛ ጊዜ ይከበራል፡፡ በዓላቱ በአገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ሲከበሩ ይዘዋቸው የተነሱት መሪ ቃሎች ምን ነበሩ) በዓላቱ በየትኞቹ ከተሞች ተከበሩ) እስቲ ወደ ኋላ መለስ ብለን እናስታውስ፡፡

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በአዲስ አበባ ሲከበር መሪ ቃሉ "ህገመንግሥታዊ ቃል ኪዳን የአብሮነታችን መገለጫ ነው" የሚል ነበር፡፡

ቀጣዩን በዓል ያስተናገደችው ሐዋሳ ከተማ ነበረች፡፡ የበዓሉ መሪ ቃልም "ልዩነታችን ውበታችን፣ ውበታችን አንድነታችንና ጥንካሬያችን" የሚል ነበር፡፡

በኦሮሚያ አዘጋጅነት አዲስ አበባ ላይ የተከበረው ሦስተኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን መሪ ቃሉ "አንድነታችንን በማጠናከር ልማታችንን እናፋጥን" የሚል እንደነበር ይታወሳል፡፡

አራተኛውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀንን አፋር፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ሐረሪና ድሬዳዋ በጋራ ነበር ያዘጋጁት - በድሬዳዋ ከተማ፡፡ የበዓሉ መሪ ቃልም “መቻቻል ለዴሞክራሲያዊ አንድነትና ልማት” የሚል ነበር፡፡

ባለፈው ዓመት በአዲስ አበባ የተከበረው 5ኛው በዓል ደግሞ “የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘን የአገራችንን ህዳሴ ወደማይቀለበስበት ደረጃ እናደርሳለን” የሚል መሪ ቃል ይዞ ነበር፡፡

ይኸው በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ በመዲናችን ከተዘጋጀው 5ኛው ዓለም አቀፍ የፌዴራሊዝም ጉባዔ ጋር በተጣጣመ መልኩ መከበሩ አይዘነጋም፡፡

ዘንድሮ ለስድስተኛ ጊዜ የሚከበረውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓልን የምታስተናግደው የመቀሌ ከተማ ናት፡፡ የበዓሉ መሪ ቃልም “ህገ መንግሥታችን ለብዝሀነታችን፣ ለአንድነታችንና ለህዳሴያችን” የሚል ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ጥቅሞቻቸውን በማጐልበት አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመገንባት ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ በአንድነት ተነሳስተዋል፡፡

በብዝሀነት ላይ መሠረቱን የጣለው አንድነት ለህዳሴውም ስኬት መገለጫ ነውና የህጐች ሁሉ የበላይ የሆነውን ህገ መንግሥት ጠብቆ ለማቆየት ሁሉም በፅናት ቆሟል፡፡

በመላ ኢትዮጵያ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩበት፤ ለዴሞክራሲያዊ አንድነት መሠረት የተጣለበት፤ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት፣ ውበትና ህብረት የታየበት ብሎም የሥልጣን ባለቤት መሆናቸውም የተረጋገጠበት፣

የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጉዞ የተጀመረበት መሠረቱ ይኸው ህገ መንግሥት ነው፡፡

የህገ መንግሥቱ ድሎችና ውጤቶች ከመቼውም በላይ ተስፋፍተው፤ የዜጐች ማንነትና ባህላዊ እሴቶች ጐልተው ወጥተው፤ መልካም ተሞክሮዎችም ይበልጡን ጐልብተው የአንድነታችንና የጥንካሬያችን መገለጫ ሆነው እንዲቀጥሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው ጉዟቸውን ቀጥለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት ሕገ መንግሥቱ ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለ 17 ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

በእነዚህ ጊዜያት የክልሎችን እኩል ተጠቃሚነት በማረጋገጥ በኩል በተለይም በልማትና ዕድገት አፈፃፀም ረገድ በጎ እርምጃዎች ተወስደው፤ መልካም ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው እኩል የመልማት መብት በመጠቀም በሁሉም ክልሎች በተነፃፃሪ ፈጣን የሚባል ልማትና ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ ሕብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓት ከአገሪቱ ተጨባጭ ታሪካዊ ሁኔታ በመነሳት በሕገ መንግሥቱ ተደንግጎ ተግባራዊ መሆንም ጀምሯል፡፡

ሕብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓቱ ያለፉት አፋኝ መንግሥታት የቀበሩትን የማንነትና የምጣኔ ሀብት ተጠቃሚነት ጥያቄን በአስተማማኝ ደረጃ መመለስ ችሏል፡፡

በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነትን ለማስቀጠልና ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ቃል ኪዳን ያሰሩበትን አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባት ጉዳይ በህዳሴው እየተቀላጠፈ ይገኛል፡፡

የፌዴራል ሥርዓቱ ባልተማከለ አስተዳደር ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው በማስተዳደር ማዕቀፍ ውስጥ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲኖራቸው አስችሏል፡፡

በዚህም ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ተሳትፎአቸውና በየደረጃው ተጠቃሚነታቸው ጎልብቷል፡፡ አካባቢያቸውንም በማልማት ለአገር ብልፅግናና እድገት ከፍተኛ ድርሻ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

የክልሎችን የእኩል ተጠቃሚነት በማረጋገጥ አንፃር ደግሞ የልማትና ዕድገት አፈፃፀም በክልሎች እኩል ተጠቃሚነት እየተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ እውነታ ነው፡፡

የክልሎችን የእኩል ተጠቃሚነት በማረጋገጥ አንፃር ልማታዊው መንግሥት ግልፅ የሆኑ ምጣኔ ሀብታዊ ሕጎችን፣ የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ነድፎ በየአካባቢው ተጨባጭ እቅድ እየተመነዘሩ የሚፈፀሙበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

በአፈፃፀም ሂደት የተገኙ በጐ ልምዶችም እየተቀመሩ በአገሪቱ ሁሉም አካባቢዎችና ለምልዓተ ሕዝቡ የሚደርስበት ስልቶች ተቀይሰዋል፡፡

የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመተግበር ዙሪያ የሚያጋጥሙ ማነቆዎች የሚለዩበትን የአሰራርና የአደረጃጀት ጥያቄዎች ካለፉት ልምዶች በመነሳት እንዲፈቱና እንዲስተካከሉ በማድረግ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የላቀ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እየተረጋገጠ ይገኛል፡፡

ክልሎች በገጠርና ከተማ የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅዶችን በመንደፍና ሕዝቦቻቸውን ዋናው ፈፃሚ አካል በማድረግ ባለፉት ስምንት ዓመታት በአማካይ ለተመዘገበው ከ11 በመቶ በላይ እድገት የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ አግዟል፡፡

የፌዴራል መንግሥትም ክልሎችን ከክልሎች ብሎም ከአዋሳኝ አገሮች ጋር የሚያገናኙ መንገዶችን በመስራትና ፈጣን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን በማዳረስ ላይ ይገኛል፡፡

እንዲሁም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን በማፋጠን፣ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትንና የአገር ውስጥና የውጭ አገር የገቢያ ትስስርን በመፍጠርና በማጐልበት አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባቱ ግብ በአስተማማኝ ሁኔታ እየተተገበረ ይገኛል፡፡

የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ይህንኑ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ወደ ላቀ ደረጃ በሚያሸጋግር መልኩ ተቀይሶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በአገሪቱ ያሉ ክልሎች እርስ በርስ በመደጋገፍና ልምዶችን በመለዋወጥ የሚያደርጉት የጐንዮሽ ይሁን የተዋረድ ግንኙነት ለእኩል ተጠቃሚነትና በተመጣጣኝ ልማትና ዕድገት ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

የልማትና የመልካም አስተዳደር ማነቆዎችን በመፍታትና በጐ ልምዶችን በማስፋፋት ሂደቱን ማስቀጠል ከተቻለ አጭር በሚባል ጊዜ ውስጥ አገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ የማትሰለፍበት አንዳች ምክንያት አይኖርም፡፡

እዚህ ላይ የልዩ ድጋፍ ክልሎችን አቅም የመገንባቱ ሥራ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መቃኘቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች በታሪክ አጋጣሚ በአገሪቱ ዳር ድንበር ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ምንም ዓይነት የሰው ኃይል፣ የማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማትና የመሠረተ ልማት አውታሮች ያልተሞከረባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ አገሪቱ

በአጠቃላይ ከተዘፈቀችበት ድህነትና ኋላ ቀርነት በባሰ ደረጃ ስር ሰዶ የቆየባቸው አካባቢዎችም ነበሩ፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ላይ እንደተደነገገው እነዚህ ክልሎች በአሁኑ ወቅት ፖለቲካዊ መብቶቻቸውን እንደተቀሩት የአገሪቱ ክልሎች አስከብረዋል፡፡

ራሳቸውን በራሳቸው ከማስተዳደር ጀምሮ አካባቢያቸውን በማልማትና ሕዝቦቻቸውን የሠላም፣ የልማት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚዎች ለማድረግ እየተረባረቡም ይገኛሉ፡፡

በግልጽ አይቶ መፍረድ እንደሚቻለው በእነዚህ ክልሎች ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ተቋማትና የመሠረተ ልማት አውታሮች በሚያስደንቅ ፍጥነት እየተገነቡ ነው፡፡

የሰው ኃይል ልማት በራሳቸውና በፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ እየጨመረ በሚሄድ ቁጥር በየዓመቱ እየገቡና እየተመረቁ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎችን የማስፈፀም አቅም በመገንባት ላይም ናቸው፡፡

ዛሬ አካባቢዎቹ ከየትኛውም ጊዜ በላይ ሠላማዊ ሆነዋል፡፡ የመሠረተ ልማት ዝርጋታውም እየተሟላ ሄዷል፡፡ ለክልሎቹ ምርት፣ ምርታማነትና የገበያ ትስስር ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ አካባቢዎቹ በልማትና እድገት ጎዳና እየተራመዱ ይገኛሉ፡፡

ይህም በአካባቢዎቹ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር፣ የሥራ እድል እንዲፈጠርና ነዋሪዎቹ ተጨማሪ የገቢ እድል የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ ነው፡፡

የክልሎቹ መንግሥታትና ሕዝቡ ከሚያደርጋቸው ልማታዊ ርብርብ ጐን ለጐን በፌዴራል መንግሥት በኩል የተለያዩ ተገቢነት ያላቸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ሚኒስትሮች የሚገኙበት የልዩ ዕገዛ ቦርድ ተቋቁሟል፡፡

ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የተገኙ ሰነዶች እንደሚያስረዱት የአጐራባች ክልሎች የልማት ትብብር ፕሮግራም በመንደፍና የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች የሚያሳኩ የበጀት አመዳደብና ድጋፍ ሥርዓቶችን የመዘርጋት ዘላቂ አቅም የመገንባት ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡

እስካሁን የተገኙ ውጤቶች አበረታች መሆናቸው እንደተጠበቁ ሆነው ለቀጣዩም መሠረት ስለሚጥሉ የፌዴራልና የክልሎች መንግሥታት የጋራ ርብርብ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በተለይ በእነዚህ ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ውስጥ በቅርቡ የተጀመረውና እየተከናወነ ያለውን በመንደር የማሰባሰብ ፕሮግራም በጥቂቱ እንዳስስ፡፡

በመንደር የማሰባሰብ ፕሮግራም ዓላማው ዜጎች ከአገራቸው ልማትና እድገት በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አካል እንዲሆኑ ለማስቻል ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ፕሮግራሙ በአገሪቱ የመልካም አስተዳደር፣ ዴሞክራሲና የልማት መብቶችን ለማስጠበቅ የሚከናወን ነው፡፡

በዴሞክራሲያዊ መብት ረገድ ዜጎች ተበታትነው በሚኖሩበት ሁኔታ የተደራጀ ትግል ሊያካሂዱ ይሁን ድምፃቸውን ሊያሰሙ ያዳግታቸዋል፡፡

በመሆኑም ዜጎች ተበታትነው ከሚኖሩበት ሁኔታ ወጥተው በመንደር መሰባሰባቸው ወደሚችሉበት ሁኔታ የሚያመጣ ነው፡፡

መብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው ዙሪያ እንደ ሕዝብ ድርሻቸውን ሊወጡም ይሁን ከመንግሥት መዋቅር ጋር በቅርበት ለመወያየትና መፍትሄ ለማፈላለግ ያስችላቸዋል፡፡

ይህ ፕሮግራም ከአገሪቱ አቅም ተነስተን ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማቅረብ ያስቻለ ነው፡፡

የዜጎችን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ረገድ ከወዲሁ ከፍተኛ ውጤት መታየት ጀምሯል፡፡ ይህ ፕሮግራም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እየተከሰተ ከሚገኘው የአየር ንብረት ለውጥና ከሚያስከትለው አደጋ ዜጎችን የመታደግ ዓላማም አለው ፡፡

በዚህ ዓላማ መሠረት ባለፈው ዓመት በሶማሌ፣ በጋምቤላና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች 126 ሺህ ቤተሰቦችን በመንደር ለማስባሰብ ተችሏል፡፡ በዚህ ዓመት ደግሞ በእነዚሁ ክልሎች ውስጥ 127 ሺህ ቤተሰቦችን ለማሳበሰብ ዕቅድ ተይዟል፤ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችም እየተጠናቀቁ ይገኛል፡፡

ሕዝቡ በሚሰባሰብበት ወቅት ከሁሉም በላይ ከዴሞክራሲያዊ መርሆዎች በመነሳት በሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሚፈፀም ፕሮግራም ነው፡፡ በየአካባቢያዎቹ በቂ የጓሮ፣ የእርሻ፣ የግጦሽ መሬትና የውኃ አቅርቦት መኖሩን በማረጋገጥ ጭምር፡፡

በፕሮግራሙ ላይ ሕዝቡ የተረጂነትና የጠባቂነት አስተሳሰብ ሳይሸከም ወደ ምርት ተግባር እንዲሸጋገር የሚያስችሉ የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት አቅርቦት ሥራዎች ጎን ለጎን እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ማህበራዊ የመሠረተ ልማት ተቋማት እየተገነቡ በአገልግሎት ላይ የዋሉበት ሁኔታም ተፈጥሯል፡፡

ይህ በመንደር የማሰባሰብ ኘሮግራም በሌላ በኩል በልዩ ድጋፍ ክልሎች ያሉ ሕዝቦች በሠላም፣ በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ያላቸውን ተሳትፎ በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በዚህም ሂደት በክልሎች መካከል ያለውን የተመጣጠነ ልማትና ዕድገት ዓላማ እያሳካ የሚገኝ ፕሮግራም ነው፡፡

ይህ ኘሮግራም በተነፃፃሪ እጅግ ባጠረ ጊዜ የዜጎችን የአኗኗር ዘይቤና የኑሮ ደረጃ ከመሠረቱ የሚቀይር መሆኑ ይታመናል፡፡ ይሁንና ዕቅዱ ተሳክቶ ማየት የማይፈልጉና የራሳቸው ዓላማ ያላቸው አካላት ኘሮግራሙን ለማደናቀፍ የተለያዩ ሰበቦችን በመደርደር የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡

እነዚህ ወገኖች ድህነትና ኋላ ቀርነት መገለጫችን ሆኖ እንዲቀጥል የሚፈልጉ ብሎም ለራሳቸው የቱሪዝም መዳረሻ፣ የድህነትና የችግር ጥናትና ምርምር ጣቢያዎች ሆነን ለዘለዓለሙ እንድንዘልቅ የሚሹ ጭምር ናቸው፡፡

የመንደር ማሰባሰቡ ፕሮግራም በማስገደድ የሚፈፀም፣ ዜጎችን በማፈናቀል ለኢንቨስትመንት መሬት የሚያስለቅቅ፣ በአካባቢዎቹ ደንና ዱር እንስሳት ላይ አደጋ እያደረሰ እንደሆነ በማስመሰል የክስ ዝርዝር የሚደረድሩበት ሁኔታም ይስተዋላል፡፡

ይህ ኘሮግራም በሙሉ ፈቃደኝነት የሚካሄድ፣ ዜጎች በግዴታ የሚፈናቀሉበት ሳይሆን ይልቁንም ጥቅም ላይ ያልዋለ ሰፊ ለም መሬት፣ የገፀ ምድርና ከርሰ ምድር ውኃ ያለባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡

እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው ዐቢይ ቁም ነገር አለ፡፡ ይ,ውም በመንደር ለሚሰባሰቡ ዜጎች፣ ለአየር ንብረት ክብካቤም ይሁን ለደንና ዱር አራዊት ጥበቃ አጉል አሳቢዎቹ ከመንግሥት በላይ ለሕዝቡ መቆርቆር እንደማይችሉ ነው፡፡

«መረረም፣ ጎመዘዘም´ ይህ ኘሮግራም ዜጎች እንደተቀረው የአገሪቱ ሕዝቦች የልማትና የብልፅግና ውጤቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ ተመጣጣኝ ዕድገት የሚመጣበት በመሆኑ ሂደቱ ተጠናክሮ ይቀጥላል ፡፡

ይህች የጋራ መኖሪያችን የምንላት ኢትዮጵያ - አበቃላት ፤ ተፈረካከሰች፤ አገሪቱም - አከተመላት፤ ዜጎች እርስ በርሳቸው ሊናቆሩ ተዘገጃጁ፤ አገሪቱም በማያበራ ግጭት ውስጥ ልትዘፈቅ ተሰነዳዳች፡፡ ሜዳዎቿ፣ መንገዶቿ በደም ጉርፍ ሊታጠቡ ቀናት ቀሯት፤ ብዙዎች ሟረቱባት፡፡ ክፉ አሳቢዎች ተሳለቁባት፡፡ መጥፎ መጥፎው ይደርስባት ዘንድም ተመኙላት፡፡

እነሆ ግና የታሰበው አልሆነም፡፡ የተፈራው አልደረሰም፡፡ መጥፎ አላሚዎች ምኞታቸው አልሰመረም፡፡ ክፉ አሳቢዎች ናቸውና ሕልማቸውም ቢሆን አልያዘላቸውም፡፡

ይልቁንም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አዲስ ምዕራፍ ገለጡ፡፡ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ፤ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች የተከበሩባት አዲስ አገር በጋራ ስምምነት አሀዱ ብለው ለመገንባት ቃል ኪዳናቸውን አሰሩ - ለዚያውም በደም ቀለም የተፃፈ ቃል ኪዳን፡፡

ተማምለውም አልቀሩም፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትን መሠረቱ፡፡ ዋስትና ይሆናቸው ዘንድም በደም ቀለም የተፃፈውን ሕገ መንግሥታቸውን በፅናት ሊጠብቁ በእምነት ቃል ተገባቡ፡፡ እነሆ ፍሬውን ማጣጣምን ያዙ - የነገ ሰው ይበለን ፡፡